ዝንቱ ውእቱ ትእምርተ ሰላም፤

ዘረሰዮሙ አሐደ ለክልኤሆሙ ፤ ኤፌ ም ፪ ቍ ፲፬

፲፰ኛ ዓመት ቍጥር ፲፮

አ ፡ አ ፡ ሚያዝያ ፳፪ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

# ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

ይህ ድርሰት ለሃይማኖትና ለምግባር ለጊዜውም ዜና መዋዕል መግለጫ የንባቡን ቀጥተኛ ትርጓሜ ከመከተል ጋር ስለ ታላቁ ኢትዮጵያዊ ሐዋርያ መታሰቢያ ተክለ ሃይማኖት ተብሎ ተሰየመ ።

የድርሰቱ ዋጋ ባገር ውስጥ ባመት ብር 1.20
» » አንዱ 0.5
ለውጭ አገር እጥፍ ፣ ሆናል ።

በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የታሪክና ዜና ማኅደራዊ ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት ታተመ ።

በወር ሁለት ጊዜ ይወጣል ።
የስልክ ቍጥር 130901
የፖስታ ሳጥን ቍጥር 12.83

## በመስቀል ባፈሰሰው ደሙ ይቅርታ አደረገልን ፤

ከአባ ተፈራ መልሴ

የይቅርታ ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ ዓለም በሙሉ በይቅርታ መርከብ እንደሚንሳፈፍ ሲያስረዳ ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆላስይስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ "ወበቱ ይማሃሎ ለኵሉ ወገብረ ሰላመ በደመ መስቀሉ ለዘበሰማይ ወለዘበምድር ። ሁሉንም በሱ ይቅር ይለው ዘንድ በመስቀል በፈሰሰው ደሙ በሰማይ ያሉትንና በምድር ያሉትን አስታረቀ እናንተም ቀድሞ በልባችሁ አሳብ በሥራችሁትም ክፉት ነሱ የተለያችሁ ጠላቶቹ ነበራችሁ ዛሬ ግን ይቅር ብሏችኋል በተቀበለው መከራውና በሞቱ ከፊቱ ለመቆም የተመረጣችሁ ንጹሐን ክቡራን ያደርጋችሁ ዘንድ» ሲል ይናገራል ቆላ ፩ ፲፱ ሐዋርያው እንደተናገረው በመስቀል ላይ በፈሰሰው ደሙ ፍጹም ይቅርታን አግኝተን ወደተስፋው ቀርበናል፤ በኃጢአት ከመገዛት ነፃ ወጥተን ወደ ጌትነት ተመልሰናል፤ አስታራቂያችን ኢየሱስ ክርስቶስ የዋላጅውንም መጋረጃ ቀዶ የድኅነት በር ከፍቶልናል፤ ርቀን የነበርነውን በጌትነቱ ወደ አባቱ አቀረበን ፤ ኃጢአታችንን አስወግዶ በጽድቅ መንገድ መራን፤ በሱ ቁስል እኛ ተፈወስን በጠቅላላው የይቅርታ ልጆች ስለሆን በምድር ላይ ሰላምን መሠረተልን ። በሁሉተኛውም ምዕራፍ ቁጥር አሥራአራት ላይ በሠራው ሥራት የዕዳችንን ደብዳቤ ከባላጋራችን እጅ አጠፋልን ከመከከላችን አራቀው ፤ በመስቀሉም ቸንከረው ፤ ልብሱን በመገፈፉና ዕራቁቱን በመቆሙ የቀደሙትን ገዥዎች አሳፈራቸው ይላል ቆላ ፪ ፲፬ ቅዱስ ጳውሎስ የክርስቶስ ወገኖች ለሆነው ሁሉ ተወዳጅ ምክሩን ሲያበረክት ክርስቶስ በሠራው ሥራት በተቀበለው መከራ የዕዳችንን ደብዳቤ ከባላጋራችን እጅ አጠፋልን፤ ከመከከላችን አራቀው፤ በመስቀሉም ቸንከረው በደላችንን ሁሉ ይቅር ብሎ መለያየትን አስወግዶ በአንድነት ሰበሰበን ፤ ጠላታችንን ሰይጣንን አጠፋልን ጠላቶቹ ስንሆን ወገኖቹ አደረገን እያለ ይናገራል ይህ ሁሉ ኢየሱስ ክርስቶስ ለሰው ልጅ ያደረገው ትድግና ነው። እሱ በደስታ ላይ ደስታ ፣ በክብር ላይ ክብር አጎናጸፈን እኛስ ለፈጣሪያችን ኢየሱስ ክርስቶስ ምን ለማድረግ መዘጋጀት አለብን? እሱ ራሱ እኔ ያደረግሁላችሁን ተመልክታችሁ እኔ እንዳደረግሁላችሁ እናንተም ለወንድሞቻችሁ እንዲሁ አድርጉላቸው ያለውን አምላካዊ ቃል ተገንዝበን እርስ በራሳችን መተሳሰብ ፤ ወንድሜ ወንድሜ መበባል ፣ ለኛ ለወገኖቹ ሲል መራራ ሞትን መቀበሉን ማሰብ ያስፈልገናል። ይህን ካደረግን ሌላ የምን ጠየቅበት ስለሌለ ከፍ ያለ የይቅርታ ዋጋ እናገኛለን ። ይኸውም ፩ኛ በፍጹም ልብህ በፍጹም አሳብህ ፈጣሪህን አምላክህ (ውደድ) ፪ኛ ወንድምህን እንደራስህ ውደድ ያለው ቃል ሕጎችን ሁሉ ሰለሚፈጽም ይህን ከፈጸምን ዋጋ እናገኛለን ስለዚህ እሱ የይቅርታ አምላክ ስለሆነ እኛም ለዘለዓለም የይቅርታ ልጆች ለመሆን እንድንችል አበቦችን ሳይረግፍ፤ ቀኑ ሳይመሽብን ይህ ዓለም የዝግጅት ዓለም መሆኑን አውቀን አሁኑኑ እንዘጋጅ ።

## ጸሎተ ሐሙስ

ከመ. መልአኩ ፈለቀ ።

ክርስቶስ ከፋሲካ በዓል አስቀድሞ በነበረው በዓል ደቀ መዛሙርቱን አዘዛቸው ። እነሱም ወደ እርሱ ቀርበው ፋሲካውን ትበላ ዘንድ በየት ልናዘጋጅልህ ትወዳለህ ? ብለው ጠየቁት ።

ከከተማው ወጣ ብላችሁ ወደ ገሊላ አጠገብ አንድ ባለጸጋ ሰው አልዓዛር የተባለ አለና ሒዱችሁ ንገሩት አላቸው ። እነሱም ወዲያውኑ ፈጥነው ሒደው መምህር ጊዜዬ ደርሷልና ከደቀ መዛሙርቴ ጋራ በአንተ ቤት እውላለሁ ብሎሃል ብለው ነገሩት ። እሱም በጣም ተደሰተና ቤቱን አነጣጥሮና ጉዝጉዞ ሲጠባበቅ ፣ ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን አስከትሎ ከዚያ ባለ ጸጋ ቤት ደረሰ ። ያም ባለ ጸጋ እጅ ነሥቶ ፈጣሪውን በክብር እንግድነት ተቀበለ ።

ጌታችንም ከዚያ ሰው ቤት እንደ ዋለ ሁሉም የከተማውም ሕዝብ አውቀውታል ። ምክንያቱም የሱ ተማሪ የነበረው ይሁዳ ከአይሁድ አለቆች ጋራ ተዋውሎ በ፴ ብር አሸጥላችኋለሁ ብሎ በስነበር እነሆ ክርስቶስ ከዚህ ቤት ገብቷል አሁንም ከዚሁ ቤት አለ እያለ ለከተማው ሕዝብና ለባለ ሥልጣኖቹም ይነግራቸውና ያስጠናቸው ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜው ሲደርስ ግን ክርስቶስ ደቀ መዘሙርቱን ዙርያውን አሰልፎና አስቀምጦ በአጭር ታጥቆ ማለት ፊቃኑን ነብሶ ፤ ወገቡን በዝናር ታጥቆ ፤ በንበቷራ ውኃውን መልቶ እግራቸውን እጃቸውን ሊያጥብ ተነሣ ። ከመከከላቸው አንዱ ቅዱስ ጴጥሮስ አይሆንም ቢለው እኔ ካላጠብኩህማ ክብር የለህም ብሎ ተስፋውን ገልጾ ነግሮታል ።አቤቱ ፈጣሪዬ ስንኳን እግሬን እጄንም ፤ መላ ሰውነቴንም እጠበኝ አለው ። ወዲያው ከጴጥሮስ ጀምሮ መላውን ሐዋርያት እያንዳ አንዳቸው አጥቧቸዋል ።

ከዚህ በኋላ ኅብስቱንና ጽዋዉን አንስቶ ፤ አክብሮ ፤ ለውጦ ነገ በመልዕልተ መስቀል የሚፈተተውና የሚፈሰው ሥጋዬና ደሜ ይህ ነው ንሡ ብሉ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው ።

እነሱም ሳይጠራጠሩ አማናዊ ሥጋውና አማናዊ ደሙ መሆኑን ተረድተው በክብር ተቀብለውታል ። እሱ ራሱ ሲያስተምር «ሥጋዬን የበላ ፤ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወትን ያገኛል አለዚያ ግን ከኔ ክፍል የለውም» ብሎ በአደባባይ ሲናገረውና ሲያስተምረው ስለ ነበር በዚህን ጊዜ ተፈጸመ ለማለት ይቻላል ።

ሐዋርያትም ይህን ተቀብለው በአእምሮ ጐለመሱ ፤ ከብልየትም ታደሱ ። ለዚሁም ሥርዓት መደበኞች ሆኑ ።

# ቅድስት ኢየሩሳሌም

ከአባ ተፈራ መልሴ ።

ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ሀገረ እግዚአብሔር የተባለች የተመረጠች ሀገር ናት ።

ይህችውም ሀገር ትንቢት የተነገረባት ፤ ሱባዔ የተቈጠረባት ፤ ታላላቅ ነገሥታት የነገሡባት ፤ ብዙዎች ነቢያቶች ተነሥተው ስለክርስቶስ ትንቢት የተናገሩባት ጽርሐ ንጽሕት ሀገር ከመሆኗም በላይ አምላክ ሰው ፤ ሰው አምላክ የሆነባት ናት ።

የዓለሙ መድኀን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም ከቅድስት ድንግል ማርያም ከተወለደ ጀምሮ ለዘመዶቹ እየታዘዘ ፤ ልዩ ልዩ ተአምራት እያደረገ እስከ ፴ ዓመት ድረስ የተቀመጠው በዚችው ሀገር ነው ።

ከዚያም በኋላ ዮርዳኖስ በሚባለው ታላቅ ወንዝ በዮሐንስ እጅ ተጠምቆ ፤ ፵ ቀንና ፵ ሌሊት ጾሞ ፤ ፫ ዓመት ከ፫ ወር አስተምሮ የነገሠባት ሀገር እንደ መሆኗ መጠን ትንቢቱ ይፈጸም ዘንድ የሰላም ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ በታላቅ ግርማ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ የተባረከ ነው ሆሣዕና በአርያም መድኃኒት መባል ይገባዋል ተብሎ እየተመሰገነ በደስታ ፤ በይባቤ የገባው ወደዚችው ቅድስት ሀገር ነው ።

ስለዚህ ይኸች ሀገር የእግዚአብሔር ሀገር ተብላ ትጠራለች ። ምክንያቱም ፩ኛ ከአብርሃምና ከልጆቹ ጋር የተነጋገረባት ፤ ተስፋ የሰጠባትና የተስፋውን ቃል ኪዳን ያጸናባት ፤

፪ኛ ለነቢያቶች ትንቢት ያናገረባትና ትንቢቱም የተፈጸመባት ታላቅ ሀገር በመሆኗ ሀገረ እግዚአብሔር ትባላለች ፤

፫ኛ በመጨረሻው የዓለሙ ቤዛ ኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነቱን ለሕማም ለሞት አሳልፎ የሰጠባት ፤ መከራ የተቀበለበት ፤ የሱ ሞት የዓለሙ ሕይወት በመሆኑ ለዓለም ድኅነትን ያበሠረበት ፤ ከሙታን ተለይቶ የተነሣበትና የትንሣኤውን ብርሃን የገለጸበት በዚችው ማዕከለ ሀገር በሆነችው ቅድስት ሀገር ኢየሩሳሌም ነው ።

፬ኛ ለደቀ መዛሙርቱ በዝግ ቤት ገብቶ ተጨንቀው ተጠበው ሳሉ ሰላም ለሁላች ይሁን ብሎ ሰላምን ያበሰረበት ፤

፭ኛ በክብር ፤ በይባቤ መላእክት ያረገበት ፤ ለሐዋርያትም «ጽንሑ ተስፋሁ ለአብ ከአብ ዘንድ የሚመጣላችሁን ተስፋ ደጅ ጥኑ» ባለው መሠረት በ፶ኛው ቀን የወረደላቸውን መንፈስ ቅዱስን ተቀብለው በአእምሮ የጐለመሱበት ፤ በእውቀት የታደሱበት ይህችው ሀገር ናት ፤

እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያምም የምትጸልየው በዚችው ቅድስት ሀገር ነው ።

ይሁን እንጂ ስለ ኢየሩሳሌም ድርጊትና ታሪክ ሰፋ ያለ ጊዜና ብዙ ታሪክ ጸሐፊዎች ስለሚያስፈልግ በአጭሩ ለማስታወስ ያህል ከዚህ በላይ የተነገረውን መገንዘብ ያስፈልጋል ።

በዚች ቅድስት ሀገር ብዙዎች ድርጊቶች ስለተፈጸሙባት ፤ የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን የትንሣኤውን በዓል ማክበርና ልዩ ልዩ ተአምራት የተደረገባቸውን ሀገሮችና ቦታዎች ለመጎብኘት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በብዙ ድካምና ስቃይ በእግር እየተጓዙ ከብዙ አህጉራተ ዓለም ይመጡ ነበር ። ከሀገራችን ከኢትዮጵያም ፮ ወር ፯ ወር በእግር ተጉዘው ይህችን ቅድስት ሀገር ጐብኝተው ይመለሱ ነበር ።

ዛሬ ግን በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የዓመቱን ጕዳና በአንድ ቀን ለመድረስ ስለተቻለ በኢትዮጵያ ቁርስ አድርጎ ኢየሩሳሌም ምሳ ለመብላት ይደረሳል ። ስለዚህ የሀገራችን የኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ይህችን ቅድስት ሀገር ለመጎብኘት ከፍ ያለ መንፈስዊ ስሜት ስለአላቸው በየዓመቱ ወደዚች ቅድስት ሀገር እየሄዱ የትንሣኤን በዓል ያከብራሉ ። በዚህም ዓመት ወደዚች ቅድስት ቦታ ለመሄድ የሚያስቡትን የእግዚአብሔር በረከት እንዳይለያቸውና በሰላም ለመመለስ እንዲያበቃቸው ተክለ ሃይማኖት ጋዜጣችን ምኞቱን ይገልጻል ።

## የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጥሪውን ተቀበላለች ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ከግንቦት ፲፩ እስከ ፲፬ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. ድረስ በካይሮ ከተማ ላይ በሚደረገው የምስራቅ ኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ላይ እንድትገኝ ከድርጅቱ የተላለፈላትን ጥሪ የተቀበለች መሆኑን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የውጭ አገሮች መገናኛ ክፍል አስታውቋል ።

## ጉባኤ ።

በምድረ ግብፅ መናገሻ ከተማ ካይሮ ላይ ከሚያዝያ ፳ እስከ ፳፬ ቀን ፲፱፻፶፯ ዓ. ም ድረስ ለ፬ ቀናት ያህል በሚደረገው የቅርብ ምሥራቅ ክርስቲያን ካንሰል ጉባኤ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተካፋይ ሆናለች ።

www.ethiopianorthodox.org

ነበእኬ ንሕነ እከኑ መሬት ከመ ሐሰር
ዘቅድመ ገጸ አሳት ድልዋኒከሙ ንበሩ
እስመ ኢተአምሩ ኢትፍርህዋ ለሞት
ፍርህዋ ለኃጢአት ።
የጸሎትን መንገድ ጥርጊያውን ይዘህ ፤
እንቅፋት ሳይመታህ እሾህ ሳይወጋህ ፤
ደህና ትገባለህ ገነት ከቤትህ ።
በራሴ መስዮ ይኸንን የጻፍሁት ፥
ለሁላችንም ነው ምሥጢሩን ስታዩት ።

የመናገሻ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን አስተዳዳሪ አለቃ ወልደ ማርያም ሁብቴ ።

# መልእክት

## ለዛሬዪቱ ቤተ ክህነት ።

ቤተ ክህነት እርምጃዋን አሳምራ ነቃ ነቃ ማለት በመጀመርዋ ያልተደሰተ ፍጡር በኢትዮጵያና እንዲሁም በልዩ ልዩ አህጉር ያሉት ዜጎች አሉ ለማለት አያስደፍርም ። ብዙ ሊነገሩ የማይችሉ ችግሮች ገጥመዋት ነበር። አሁን ግን ችግሩ እየተቃለለ በመሄዱ እግዚአብሔር አምላካችንን ልናመሰግነው ይገባናል ። ይኸንንም ስናገር ኢትዮጵያን የሚጠብቀው እግዚአብሔር አምላክ ብቻ እንጂ በጦርመሣሪያ ኀይል አለመሆኑንምጭምር ስንገነዘብ ከቶ የሥጋ ቅጣትን ልንፈራ አይገባንም። የእውነት መምህራን እንደመሆናችን መጠን እውነትን ይዘን እስከ መጨረሻው እንደክማለን። እናንተም በርቱ እኛም በለንበት እንታገላለን፤«ያለውን ከወረወረ ፈሪ አይባልም» የሚል የአበቶች ታሪክ አለ ስለዚህ ሁላችንም በየተመሣራን በት ሥራችንን ከከናወን የቤተ ክርስቲያናችንን ችግር ልናቃልላት እንችላለን ። ታላቁ ሊቅ ሰሎሞን «ለሁሉም ጊዜ አለው» ብሏል ። ይሁን እንጂ የጊዜው መሣሪያ ሕይወታችን ስለሆነ ለማንኛውም እንቅፋት ጊዜ መስጠት አያስፈልግም አሁኑኑ መሥራት ነው። ሕይወትን ለሥራ መስጠት ያሻል ድምጻችሁ ጐላ ጐላ እያለ በመሰማቱ በጣም ተደስተናል በርቱ በርቱ በርቱ። ተውህበ ም ሕረት ፋንታ እንዳ ዮ ላሴ

# የዓለም ታላላቅ

## ሃይማኖቶች መሠረቶችና ተከተዩዎቻቸው ።

ከዳቤ ገጽ ዘ ጮዶ

፩ኛ ሀ. የክርስቶስ ተዋሕዶ ኦርቶዶክስ

ለ. የምሥራቅ ኦርቶዶክስ

ሐ. የካቶሊክ

መ. የፕሮቴስታንትና ኦርቤንቴስት የክርስትና እምነት ክፍል ሲሆኑ የተከታዮቻቸውም ብዛት ከ፰፻--፱፻ ሚሊዮን ይሆናል ።

፪ኛ ሀ. የአይሁድ ሃይማኖት

ለ. የእስላም ሃይማኖት

የተከታዮቻቸው ብዛት የአይሁድ ከ፲፪—፲፯ሚሊዮን ፤ የእስላምከ፬፻፵፭ -፶፻ሚሊዮን ይደርሳል ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት በአንዱ አምላክ የሚአመልኩና እግዚአብሔር መኖሩን የሚያምኑ ናቸው ሆኖም በመካከላቸው ልዩነት መኖሩ የታወቀ ነው ። ክርስቲያኖች የክርስቶስን መውረድ ፣ መወለዱን የሥላሴን አንነትና ሦነት ሲያምኑ ፥ አይሁድና እስላሞች በዚህ ዓይነት ትምህርት አያምኑም ግን ሁሉም በፈረንጆች ቋንቋ ሞኖቴይስትስ (monotheists) ይባላሉ ይህም በአንዱ አምላክ የሚያመልኩ ማለት ነው ።

፫ኛ ሀ. የኮንፊውሽስ ትምህርትና ተከታዮቹ ከ፫፻-፬፻ ሚሊዮን

ለ. የቡዲህስት ትምህርትና ተከታዮቹ ከ፲፭-፪፻ ሚሊዮን

ሐ. የሂንዱስ ትምህርትና ተከታዮች ከ፳፫ ሚሊዮን በላይ

መ. የቶይስት ትምህርትና ተከታዮች ፶ ሚሊዮን

ሠ. የሺንቶይስት ትምህርትና ተከታዮች ፳፭ ሚሊዮን ፤

ረ. አረማውያን ፹ ሚሊዮን ይሆናሉ ፥ እነዚህም ፖሊቴይስትስ (Polytheists) ይባላሉ በብዙ አማልክት የሚያመልኩ ማለት ነው ። እንደዚሁም ሃይማኖት የሌላቸው አቴይስትስ (Atheists) የሚባሉ አሉ ብዛታቸው ፫ ሚሊዮን ይሆናል ።

## የሚገኙበቸው አገሮች።

ብዙዎቹ ክርስቲያኖች በአውሮፓና አሜሪካ አህጉርሲገኙ ፥ የቀሩት ደግሞ በአፍሪካና በእስያ ይገኛሉ ። የቡዲህስት፤ የሂንዱላ የኮንፊውሽስ ፤ የቶይስት ፤ የሺንቶይስት እምነቶች ተከታዮች በእስያ ምሥራቅ፤በጃፓን በቻይና . . . . . በሕንድ ይገኛሉ ። የእስላም ሃይማኖት ተከታዮች ደግሞ (መሐመዳውያን) በርከት ያሉት በሕንድና በታናሽ እስያ ፤ የቀሩት ደግሞ ግማሾቹ በአፍሪካ ፤ ግማሾቹ በምሥራቅ እስያ ፤ ጥቂቶቹ ደግሞ በአውሮፓ በባልካን አገሮች ፤

(ዩጐዝላቢያ ፤ ሩማንያ ፤ ቡልጋርያ፤ አልባንያ ግሪክና የአውሮፓ ቱርክ) ነው ።

አረማውያን ፤ በሐዩ በሜሬቃ በከ ዋክብት ፥ በእባብ በዛፉ በድንጋይ በእንጨት . . . የሚያመልኩ ግማሾቹ በእስያ ፤ የቀሩት በአፍሪካና በአውስትራልየ ይገኛሉ ፤ አይሁድ በፓለስታይን (ፍልስጥኤም) በአገራቸውና እንዲሁም በአውሮፓና በአሜሪካ ተሰደው ይኖራሉ ። ሃይማኖት የሌላቸው ከሃዲዎች (አቴይስትስ) በጠቅላላው በፈረንጆች አገር የሚገኙ ሰዎች ናቸው ፤ በየአንዳንዱም በታ አልፎ አልፎም ቢገኙ በጣም ጥቂቶች ናቸው ።

ስለ እየአንዳንዱ እምነት ዝርዝር ወደፊት እቀጥላለሁ ።

ይቀጥላል ።

# የአይሁድ

## የዳስ በዓል ።

ከዚህ በኋላ ክርስቶስ ወደ ገሊላ ይመላለስ ስለ ነበር ወደ ምድረ ይሁዳ ይሄድ ዘንድ አልወደደም አይሁድ ይገሉት ዘንድ ይሹት ነበርና ዳስም የሚተከሉበት የአይሁድ በዓል ቀርቦ ነበር ዮሐ. ፯. ፩ ፫. ሊዋውያን ሸ፫—፴፬ አይሁድ ዳስ የሚተከሉበትና በዳስ ሆነው የሚያከብሩት በዓል ነበራቸው ። ይህን በዓል ከግብፅ ከወጡ ጀምሮ እስከ ክርስቶስ መምጣት ድረስ ያከብሩት ነበር ፤ ምክንያቱም መጀመሪያ ከፈርዖን አገዛዝ ፥ ቀጥሎም በሕረ ኤርትራን ከፍሎ ስለ አሻገራቸው መታሰቢያ የሆን ዘንድ በዓመት በዓመት በዚሁ ዳስ ሁነው እግዚአብሔርን ያመሰግኑ ነበር ፤ ይኸውም የዳስ በዓል በዓለ መጸለት ይባላል ።

ስለዚህ ይህ በዓል የሚውልበትን ብንፈልግ ሌዋውያን ምዕራፍ ሸ፫ ቍጥር ፴፬ እንመልከት ። ከዚህ በኋላ አይሁድ በበዓሉ ውስጥ ያ እኔ ክርስቶስ ነኝ የሚለው ወዴት ነው ? እያሉ ይፈልጉት ጀመር በዚያ በታ የነበሩት ሕዝቡም በሱ ምክንያት በጣም ተአወኩ ከእነሱም ውስጥ ደግ ሰው ነው የሚሉ ነበሩ ። ሌሎችም አይደለም ሕዝቡን ያስታል እንጂ ይሉ ነበር ፤ ነገር ግን አይሁድን በመፍራት ስለ እሱ ምንም በግልጥ የተናገረ የለም ። ያን ጊዜ ፈጣሪያችን ኢየሱስም በበዓሉ እኩሌታ ሲሆን ወደመቅደሱ ወጥቶ ያስተምር ነበር ፤ አይሁድም ኃይለ ቃሉን ሰምተው ይህ ሳይማር እንዴት መጻሕፍትን ያውቃል እያሉ ያደንቁ ነበር ፤ ፈጣሪያችን ክርስቶስም መልስ እንዲህ አላቸው ትምህርቴ የኔ ብቻ አይደለችም የላከኝ የበሕርይ አባቴም ናት እንጂ እያለ በነዚያት የተነገረውን በምሳሌ አስተማራቸው ።

ከመ| መልአኩ ፈለቀ ።



www.ethiopianorthodox.org